# ሽንፈት የወለደው ሽፍጥ
## ክፍል ሁለት

አዲስ ቶልቻ

በዚሁ “ሽንፈት የወለደው ሽፍጥ” በሚል ባቀረብኩት ክፍል አንድ ፅህፍ ዶ/ር ኃይሉ አርኣያ የብሄር ብሄሮችን መብት መከበር እንዲሁም የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሂደቶች ላይ ያቀረቡት ትችቶች ላይ አስተያየት መስጠቴ ይታወሳል፡፡ በዚህም ፅህፍ ሌሎች የዶ/ር ኃይሉ ትችቶች ላይ አስተያየት አሰጣለሁ፡፡

የፕሬስ ነጻነትን  ህጉን በተመለከተ፣ “የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጁ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፀደቁት ህጎች ሁሉ በተለየ፣ ሕግን የማፅደቅ የአሰራር ስርዓት የግድ ከሚለው ገደብ አልፎ ለአመታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በተደጋጋሚ ተወያይተውበት የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል። አዋጁ የዴሞክራሲ ዋነኛ መገለጫ የሆነውን ሐሳብን የመግለፅ ነፃነትን  በምንም መልኩ የሚገድብ እንዳልሆነ  የአዋጁን እያንዳንዱን አንቀጽ ማንም በማዬት በቀላሉ ሊረዳው የሚችለው ነው፡፡

ወደተግባር ስንመጣ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሰ ነገስቱና ዶ/ር ኃይሉ አንዱ ባለሟል በነበሩበት የደርግ ስርዓት ተለጉመው የኖሩ ልሣኖች ተከፍተዋል፡፡ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ድል ቢሆንም፣ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን ያረጋገጠውን ህገመንግስት እስከመቃወም የዘለቀ አሳዛኝ ዘመቻ ለማካሄድ ያዋሉትም ነበሩ፤ አሁንም አሉ፡፡

ታዲያ ሐሳብን የመግለፅ ነፃነትን ተጠቅመው፣ ይህን ነፃነትና ሌሎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን ያረጋገጠውን ህገመንግስትና ህገመንግስታዊ ስርዓት  ለአደጋ የሚያጋልጡ ሃሳቦችን ሲያናፍሱና የፈጠራ ዘገባዎች ሲያሰራጬ፣ በአመዛኙ “ከሙያ ክህሎት እጦት ነው” በሚል ግምት ችላ መባላቸው ይታወቃል፡፡

በዚህ ሁኔታ በሰላም ምድር “አገር ባሩድ ባሩድ ትሽታለች የምፅአት ቀን ቀረበ፣ አገር ፈረሰ…” እያሉ ክፉ ትንቢት አይሉት ሟርት እየተናገሩ ህዝቡን ስጋትና ጥርጣሬ እንዲያድርበት ሲያደርጉት ቆይተዋል፡፡ እርሶም (ዶ/ር ኃይሉ) የፈለጉትን ሲቸከችኩና ሲናገሩ መቆየትዎ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሁሉ የሆነው የፕሬስ ነፃነት በመከበሩ መሆኑን ያስታወሱ።

የፕሬስ ነፃነት ከታወጀበት ከ1984 ወዲህ ባሉት አመታት “ይህን አትፃፍ፣ ይህን አትናገር፣ ይህን አታንብብ ይህን አታዳምጥ …” ተብሎ በመንግስት በኩል አንዴም እገዳ ተጥሎ አያውቅም። በሌላ ወገን ግን ይህ መደረጉን እናስታውሳለን፡፡ የዶ/ር ኃይሉ ፓርቲ የነበረው የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ በ1997 ምርጫ በህዝብ ድምፅ ያገኘውን የስልጣን ውክልና

አሻፈረኝ ብሎ ዴሞክራሲያዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ስልጣን ለመመንተፍ ባወጀው የክተት አዋጅ ላይ፣ "ይህን አታንቡ፣ አታዳምጡ፣ አትመልከቱ ..." በሚል ባስተላለፈው ትዕዛዝ ይህን አሳፋሪ ድርጊት ፈፅሟል፡፡ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን፣ የፕሬስ ነፃነትን የሚገድብ ኢ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ማለት ይህ ነው፡፡

ወደ ሲቪክ ማህበራት ሁኔታ ስንመለስ፣ የሲቪክ ማህበራትን አዋጅ በተመለከተ በእነ ዶ/ር ኃይሉ በኩል የተያዘው አቋም፣ "ሲቪክ ማህበራት ለዲሞክራሲው መጎልበት አጋዥ ስለሆኑ መንቀሳቀስ ይፈቀድላቸው" የሚል ሳይሆን፣ "የኢትዮጵያውያን ብቻ ጉዳይ የሆነው የአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ የውጭ ኃይሎች ገብተው እንዲያቦኩ ይፈቀድላቸው" ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ምክንያቱም አዋጁ ኢትዮጵያውያን በሲቪክ ማህበራት የመደራጀት፣ ሲቪክ ማሕበሮቻቸው በአገሪቱ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያም የመስራት ሙሉ መብት ያላቸው መሆኑን ስለሚያረጋግጥ፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ አምባገነን ነገስታትን ጨምሮ አንዳቸውም በአገር ውስጥ ጉዳይ የውጭ ጣልቃ ገብነትን የፈቀዱ አልነበሩም፡፡ የኢትዮጵያ ነገስታት የአውሮፓ ሚሲዎናውያን በጥርጣሬ ነበር የሚመለከቱዋቸው፣ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብተው እንዲፈተፍቱ ፈቅደው አያውቁም፡፡ ይህን የሚያደርጉት፣ የሚሲዎናውያኑ ዋና ጉዳይ የኢትዮጵያ ህዝብና የአገሪቱ ሉአላዊነት ሳይሆን ለቅኝ ገዢዎች ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ልዑኮች መሆናቸውን ስለሚያውቁ ነው።

አሁን ያሉትም አለም አቀፍ ሲቪክ ማህበራትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአብዛኛው ከዚህ የፀዱ እንዳልሆኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ፣ የህዝቡ የተሻለ ህይወትና የአገሪቱ ሉዓላዊነት ዋና ጉዳያቸው አይደለም። ዋና ጉዳያቸው አደራጅተው በገንዘብ የሚደግፏቸውን ወገኖች ጥቅም ማረጋገጥ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት በምስራቅ አውሮፓ አገራት ምርጫን አስታከው የተካሄዱት ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴዎች አስረጂነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የቅርብ ግዜ ታሪካዊ ምስክሮች ናቸው፡፡

ዶ/ር ኃይሉ ባቀረቡት ጽሁፍ "የፀረሽብረ ህጉ ህዝቡን በፍርሃት እንዲጨበጥ አድርጓል" ብለዋል፡፡ በዚህ ሃሳብ ላይ ብዙ አስተያየት መስጠት አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም አንድም ሰላማዊ ኢትዮጵያዊ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉን ፈርቶት ስለማያውቅ፡፡

ህጉን የሚፈሩት አሸባሪዎችና ከሽብር ጋር የተነካኩ ብቻ ናቸው። በእርግጠኝነት ዶ/ር ኃይሉም አንድም በሰላም መኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ለአፍታም አስፈርቶት ስጋት አሳድሮበት እንደማያውቅ ልባቸው ይረዳል፡፡

ዶ/ር ኃይሉ በአገሪቷ የተመዘገበውን የኢኮኖሚ ዕድገት የተመለከተ ጉዳይም አንስተዋል፡፡ በአገሪቱ ቁሳዊ ሃብት መፈጠሩን ግን አልካዱም፡፡ ከዚህ ይልቅ እድገት ባይኖር የሚመርጠውን ቀልባቸውን ለማርካት፣ ከመሰሎቻቸው ጋር እንደፀሎት እየደገሙ የሚፅናኑበትንና እንዲሆን የሚመኙትን ተጨባጭነት የሌላው ወሬ ነው ያቀረቡት፡፡ "መንግስት የካፒታል አቅሙን እየገነባ ነው፣ በዚያውም ጥቂት ደጋፊዎቹን እያበለፀገ ነው። …" የሚል የሰለቸንን ወሬ ነግረውናል፡፡

"መንግስት የካፒታል አቅሙን እያጎለበተ ነው" በሚል ያነሱትን በተመለከተ፣ እንደሚታወቀው የመንግስት ገቢ ከግብር ብቻ የሚገኝ በመሆኑ ግብር እየሰበሰበ ነው እያሉን ነው። መንግስት ግብር በመሰብሰብ ለህዝቡ መሰረታዊ አገልግሎቶችን መስጠት፣ ወሳኝ የሆኑና የግል ባለሀብት ሊሳተፍባቸው የማይችሉ የመሰረተ ልማቶችን መገንባትና ማስፋፋት እንደሚጠበቅበት ይታወቃል፡፡

በዚህ ረገድ ከዚህ ቀደም በነበሩት ስርአቶች ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን ህዝቡን ተጠቃሚ ያደረጉ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተስፋፍተዋል፡፡ በርካታ አዳዲስ መንገዶች ተሰርተዋል፡፡ ቀደም ሲል የነበሩትም በከፍተኛ ወጪ ደረጃቸው ተሻሽሏል፡፡ ከሁለት አስርት አመታት በፊት 350 ሜጋዋት ብቻ የነበረው የኤሌትሪክ ኃይል፣ አሁን 2000 ሜጋዋት ደርሷል፡፡ ከአምስት ዓመት ወዲህ ባለ ግዜ ውስጥ ከ8000 — 10000 ሜጋ ዋት ለማድረስ በርካታ ፕሮጅክቶች በግንባታ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚደነቁ ስኬቶች እንጂ ድክመቶች አይደሉም፡፡

የመንግስት የካፒታል አቅም አሁንም መሆን ካለበትና ከሚያስፈልገው በታች መሆኑ ነው የሚታወቀው። ምክንያቱም በግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ ከጠቅላላ የአገሪቱ አመታዊ ምርትና አገልግሎት 10 በመቶ ያህል ብቻ በመሆኑ፡፡ ከኢትዮጵያ ጋር ተመጣጣኝ የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ ያሉ የአፍሪካ አገራት እንኳን የዓመታዊ ምርትና አገልግሎት ዋጋቸውን 20 በመቶ ያህል ግብር እንደሚሰበስቡ ይታወቃል። የበለፀጉት አገራት ደግሞ ከ40 በመቶ በላይ።

ዶ/ር ኃይሉ በዚህ ዙሪያ ተቃውሞ ያነሱት መንግስት ከግብር የሚያገኘው ገቢ ካደገ የሚያከናውናቸው ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሰፊ የልማት ስራዎች ከወዲሁ ስለታያቸው፣ በማደናገር የሚያገኙትን ደጋፊና አድናቂ ይቀንስብኛል በሚል ስጋት ነው።

ዶ/ር ኃይሉ "በቀን ሶስቴ ትበላለህ የተባለ ህዝብ አሁን በቀን አንዴም መብላት አልቻለም" ብለው ከኪሳቸው ያወጡትን ወሬም ነግረውናል። በእርግጥ በአለም አቀፍ ደረጃ ጭምር በተፈጠረ የኑሮ ውድነት እንዲሁም ከምግብ እህል ዋጋ መወደድ ጋር ተያይዞና ከዚህም ጋር የሃገራችንን የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ በተለይም በከተማ ኗሪዎች ዘንድ ያስከተለው የኑሮ ውድነት ጫና መኖሩ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በቀን ሶስቴ መመገብ ካለመቻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደምም በተደጋጋሚ ሲጠቀስ የነበረው ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚወክለው አርሶ አደር ነው።

ይህ የህብረተሰብ ክፍል የአገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነው ግብርና ላይ የተሰማራ ቢሆንም፣ በቀን ሶስቴ መመገብ አቅጦት መቆየቱ እውነት ነው፡፡

ይህ የሆነው በዘውዳዊው ስርዓት መሬት አልባ ጭሰኛ ሆኖ፣ ያመረተውን ባለርስቶች ከጉሮሮው ላይ እየነጠቁት፣ በኋላም ዶ/ር ኃይሉ ሲያማክሩት በነበረው የደርግ ስርዓት |የመሬት ባለቤት ነህ´ ቢባልም፤ የማምረት አቅሙን፣ የመሬቱን ለምነት፣ የአየር ንብረት ለውጥን ባላገናዘበ ሁኔታ የሚመድቡበትን የእህል ኮታ (በመጠንና በአይነት ) ለማሟላት ከጉሮሮው ነጥቆ ስለሚሰጥ፣ እየራበው አንጀቱን አስሮ ኮታውን ማሟላት እያቃተው ኑሮውን ለመደጎም በተጓዳኝ የሚያረባቸውን ከብቶች ሸጦ ዕህል ከገበያ እየሸመተ ሲያስረክብ ስለቆየ ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ምርታማነቱን ለማሳደግ እንዳይችል አድርጎ ከቆለፈው የድህነት አዙሪት ውስጥ መውጣት የሚያስችለው የገንዘብ ድጋፍ፣ የተሻለ የምርት ግብዓት አቅርቦት፣ የሙያ ድጋፍ የሚያደርግለት ባለመኖሩ፣ የሚያመርተው በቀን ሶስቴ መመገብ የሚያስችለውን ያህል እንዳይሆን አድርጎት ቆይቷል፡፡

አሁን አርሶ አደሩ ምርቱን ከጉሮሮው ላይ የሚነጥቀው ባለርስት የለበትም፡፡ መንግስት ያሰማራው የእርሻ ሰብል ድርጅት ኮታ ሰብሳቢ ግብረ ሃይልም ተወግዶለታል፡፡ ቢያንስ ሙሉ በሙሉ የምርቱ ባለቤትነቱ ተረጋግጧል።

ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት አርሶ አደሩ ምርቱን ከቀማኞች ማትረፍ ከመቻሉ በተጨማሪ የድህነት ቀለበቱን መስበር የሚያስችል አስተማማኝና ቀልጣፋ የግብርና ግብአት አቅርቦትና ተገንዘብ ብድር አገልግሎት ድጋፍ የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻችቶለታል። ከዚህ በተጨማሪም የሙያ እገዛና ክትትልም ይደረግለታል። የጤና ኤክስቴንሽን መርሃግብርና ትምህርትን ጨምሮ ሌሎችም የማህበራዊና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ያስቻሉ ፕሮግራሞች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው፡፡ ለአርሶ አደሩ እነዚህ ድጋፎች አልተደረጉም ብሎ መካድ አይን ያወጣ ውሸት ነው። አርሶ አደሩ ከዚህ ድጋፍ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም ማለት ደግሞ አርሶ አደሩ ምንም እንደማያውቅ አድርጎ እንደማሰብ ይቆጠራል፡፡

ዛሬ አርሶ አደሩ ቀደም ሲል ከነበረው በተሻለ ሁኔታ ራሱንና ቤተሰቡን እየመገበ ነው፡፡ ልጆቹን እያስተማረ ይገኛል፡፡ አብዛኞቹ አርሶ አደሮች ከሳር ጎጆ ቤት እየተላቀቁ ነው፡፡ ድሮ ለከተሜዎች ብቻ የተፈቀዱ ይመስሉ የነበሩ የፍጆታ ምርቶችንም ሸመቶ በመጠቀም ላይ ይገኛል፡፡ በመቶ ሺህ፣ በሚሊዮን የሚለካ ሃብት ለማፍራት የበቁ፣ ከአርሶ አደርነት ወደ ኢንቨስተርነት /ባለሃብትነት/ የተሸጋገሩ አረአያዎችን/ሞዴሎችን/ማፍራትም ተችሏል፡፡ እነ ዶ/ር ኃይሉ የኢትተዮጵያ ቴሌቪዥንን የሚጠሉት ይህን የአርሶ አደር የኑሮ ሁኔታ ቀዬው ድረስ ዘልቆ በማሳየት፣ የእነርሱን መርዶ ነጋሪ ሚዲያዎችን ውሸት ስለሚያጋልጥ ብቻ ነው፡፡

በዚህ እውነታ ውስጥ  ጥያቄ መነሳት ካለበት የእርሶ አደሩ ምርታማነት ከነበረበት አድጓል ወይንስ አላደገም ሳይሆን፣ “ያደገበት መጠን በቂ ነው? ፍላጎቱን ሙሉ በሙሉ ያሟላ ነው ወይንስ አይደለም? የሚል ብቻ ነው፡፡ ምርታማነቱ ማደጉ አጠያያቂ አይደለም፣ “የሚፈለገውን ያህል ነው ወይ?” የሚለውን በተመለከተ ግን መልሱ አሁንም ገና ብዙ ይቀረዋል የሚል ነው። በአጠቃላይ ዶክተር ኃይሉ በስኬቶች ላይ የከፈቱት ዘመቻ ሽንፈት የወለደው ሽፍጥ ነውና ወደ እውነታው ይምጡ እልዎታለሁ፡፡